ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 44 ሐሴ 30/2018ዓ.ም

## በውስጥ ገጾች

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከለያቸው 8 ዓበይት አጀንዳዎች መካከል አንዱ ሙስና መሆኑን አስታወቀ ገጽ 2

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ትውልድን በሥነምግባር እና በአካል የመገንባት ሀገራዊ ኃላፊነት አለበት - ክብርት ሸዊት ሻንካ ገጽ 3

የሲቪል ማህበራት ሙስናን ለመዋጋት እና መልካም አስተዳደርን ለመገንባት ያላቸው ሚና ገጽ 7

የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካለዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ ባለቤት ሁነው ይጠቁሙ!

## ሙስናን ለማጥፋት እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን የሚደረጉ ጥረቶች ተጠናክረው ይቀጥላሉ - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)





ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 30ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ በመገኘት፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በሚመለከት ከህዝብ ተወካዮች አባላት ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ሰጥተዋል። በዚህ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት ማብራሪያ፤ ሌብነት ጥዩፍ እና ቆሻሻ ነገር ነው፤ ግን ሰው እንደሚፎክረው አይደለም። በአንድ ሰው ላይ ኦዲት የተጣራ ሪፖርት አምጥቶ መንግሥት ርምጃ አልወሰደም ካለ እኔ ኃላፊነት እወስዳለሁ ብለዋል። በጥቅሉ ዝም ብሎ ፓርላማ 50 ብር አጉድሏል ማለት አይደለም፤ በተጨባጭ ማስጠየቅ የሚያስችል ጉዳይ ይቅረብ። ብዙ አሉባልታዎች አሉ፤ ሁለት መንገድ አላቸው አንደኛው ሻል ያለና ስራ የሚሰራ ሰው ከሆነ ቀላሉ ስም ማጥፊያ መንገድ ሆኖ ሰዎች የሚዘምቱበት ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ መንግሥትና ህዝብ አደራ ብሏቸው ቃለ መሓላ ፈጽመው ከዚህ ምስኪን ህዝብ የሚያጭበረብሩ አሉ ሲሉ ተናግረዋል።

ወደ ገጽ 3 የዞረ

## ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ(ፒ.ኤች.ዲ) በኢትዮጵያ የአዘርባጃን አምባሳደር ጋር ውይይት አካሄዱ



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ(ፒ.ኤች.ዲ)በኢትዮጵያ የአዘርባጃን አምባሳደር ራስላን ናሲቦቭ ጋር በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠናና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመስራት ውይይት አካሂደዋል።የመድረኩ ዓላማ የኢትዮጵያ እና የአዘርባጃን መንግስት በፀረ-ሙስና ትግል ላይ በቅንጅትና በትብብር ለመስራት የተፈራረሙትን የጋራ ስምምነት ወደ ተግባር ለማስገባት ትኩረት ያደረገ ነው።

ውይይቱ ልምድ ካላቸው የአዘርባጃን የፀረ-ሙስና ተቋማት በሥነምግባር ግንባታና የፀረ-ሙስና ትግል የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እና መልካም ተሞክሮዎችን ልምድ መውሰድ በሚቻልባቸው ላይ በጋራ መስራት ላይ ትኩረት አድርጓል።

እንዲሁም ሙስናን ለመከላከል ዲጂታል አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ በውይይቱ ተመላክቷል። የኢትዮጵያ እና የአዘርባጃን መንግስት በፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ስምምነት የካቲት 18/2018 ዓ.ም መፈራረማቸው ይታወቃል።

## የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በዓመታዊ የእቅድ አፈጻጸም ላይ ግምገማዊ ውይይት አደረጉ



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በ2018 በጀት ዓመት የእቅድ አፈጻጸም ላይ ግምገማዊ ውይይት አድርገዋል።

በግምገማዊ ውይይቱ፤ በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ የፀረ-ሙስና የህዝብ ግንዛቤ ማጎልበቻ፣ የትውልድ ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ስልጠና፣ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ማስተባበሪያ ሥራ ክፍሎች እንዲሁም በሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል፣ የሙስና መከላከል ጥናት፣ የሀብት ምዝገባና የጥቅም ግጭት መከላከል ሥራ ክፍሎች የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ቀርቧል።

እንዲሁም የዲጂታል ሙስና መረጃ አስተዳደር፣ የፀረ-ሙስና ህጎችና ዓለምአቀፍ ስምምነቶች አፈፃፀም ማስተባበሪያ እና የተቋም አቅም ግንባታ ሥራ ክፍሎች የ2018 በጀት ዓመት ውጤት አመላካች ተግባራት የእቅድ አፈፃፀም ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

ወደ ገጽ 2 የዞረ

# የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከለያቸው 8 ዓበይት አጀንዳዎች መካከል አንዱ ሙስና መሆኑን አስታወቀ

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከቀረቡለት በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ጉዳዮች መካከል ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው 8 ዓበይት አጀንዳዎችን መለየቱን አስታውቋል:: ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ የሀገር ግንባታ፣ የመንግስት አደረጃጀትና ሥርዓት፣ የፌዴራል ከተሞች አዲስ አበባ እና ድሬድዋ ከተሞች፣ የሐይማኖት፣ የተቋማት ግንባታ የህግ የበላይነት እና ሰብዓዊ መብቶች፣ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም የአርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች፣ ሙስና እና የመልካም አስተዳዳር እንዲሁም የሰላም ግንባታ የለያቸው 8 አባይት ጉዳዮች ናቸው:: እነዚህ አጀንዳዎች






በመጪው ሐምሌ 8 ቀን 2018 ዓ.ም በሚጀምረው ታላቅ ጉባኤ ላይ 130 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብን የሚወክሉ ተሳታፊዎች በሰፊው የሚመክሩባቸው ዋና ዋና ጭብጦች መሆናቸው ተገልጿል:: ኮሚሽኑ ባወጣው መግለጫ የተመረጡት 8 አጀንዳዎች በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች የተካሄዱ ሰፊና ግልጽ የውይይት ሂደቶች ውጤቶች መሆናቸውን ጠቁሟል:: በሂደቱም ከውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ከሲቪል ማኅበረሰብ፣ ከፌደራል ተቋማት እስከ ክልላዊ መንግሥታት ድረስ ሁሉም አካላት ተሳትፈዋል:: እነዚህ አጀንዳዎች ሙሉ በሙሉ የሕዝቡ ድምፅ፣ ቅሬታ፣ ተስፋ እና ፍላጎት የተንጸባረቁባቸው መሆናቸውም ተገልጿል:: የምክክሩ ስኬት የሁላችንንም በጎ ተሳትፎ ይጠይቃል ያሉት የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አረዓያ፥ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በሂደቱ ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል::

# ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አይነተኛ ሚና ይጫወታል - ክብርት ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ዘርፍ ተኮር ስልጠናዊ ውይይት አካሂዷል:: ስልጠናዊ ውይይቱ በሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭትን መከላከልና ማስተዳደር ላይ ግንዛቤ በማስጨበጥ ተቋማት ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያግዝና አመራሮች የፀረ-ሙስና ትግሉን በባለቤትነት እንዲመሩ የሚያስችል ነው::

በስልጠናዊ ውይይቱ የተገኙት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) ማንኛውም የመንግስት ተቋም የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት መወጣት የሚችለው ማህበረሰቡን በታማኝነትና በቅንነት ሲያገለግልና የተቋሙን ሀብት በቁጠባና በውጤታማነት ሲጠቀም ብቻ መሆኑን ጠቅሰዋል:: በየደረጃው የሚገኘው አመራር ራሱን ወደ ውስጥ በመመልከትና ክፍተቶቹን ፈጥኖ በማረም ለሕዝብ የሚሰጠውን አገልግሎት ለማሻሻል በሙሉ ቁርጠኝነት ሊንቀሳቀስ እንደሚገባ አሳስበዋል::







የመንግስት አገልግሎት ሪፎርም በዋናነት የህዝብን እርካታ ከፍ ለማድረግ ያለመ መሆኑን ጠቅሰው፥ በአሁኑ ወቅት የትኛውም ተቋም በትላንትናው የቢሮክራሲ አስተሳሰብ ዛሬ ላይ ውጤታማ ሊሆን ስለማይችል ሙስናና ብልሹ አሰራርን ማስወገድ የዜጎችን ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አይነተኛ ሚና ይጫወታል ብለዋል:: በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአሰራር ስርዓትን ለመዘርጋትና ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም፣አሁንም በአመራሩና በፈጻሚው ላይ የሚስተዋሉ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶችን መሙላት የግድ እንደሚል ተናግረዋል:: ሰልጣኞች በስልጠናው ያገኙትን እውቀት በስራ ክፍላቸው ላሉ ኃላፊዎችና ፈጻሚዎች በማካፈል፣ ተቋሙን ከሙስና የጸዳ፣ ተገልጋይን የሚያረካና ሀብትን በቁጠባ የሚጠቀም በማድረግ የዘላቂ ማህበራዊ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል:: የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት፤ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ! በሚል መሪ ቃል ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች ጋር በተካሄደው ስልጠናዊ ውይይት የተገኙት ተሳታፊዎች ሀሳብ፣ አስተያየቶችና ጥያቄዎች አንስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል::

## የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በዓመታዊ የእቅድ አፈጻጸም የኮሚሽኑ ...

ከገጽ 1 የዞረ

በውይይት መድረኩ በበጀት ዓመቱ የታቀዱ ውጤት አመላካች ተግበራትክፍሎች የሥራ እቅድ አፈጻጸም መነሻ አፈጻጸማቸው ጥሩ መሆኑ የተገለጸበማድረግ ሰፊ ግምገማዊ ውይይት ሲሆን፣ የበለጠ ለመስራት ቅንጅታዊየተደረገ ሲሆን፣ ከተሳታፊዎች አሰራርን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባአስተያየቶች፣ ጥያቄዎችና ሀሳቦች ተጠቁሟል:: በመድረኩ የቀረበውን የየሥራተነስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸል:: በሪፖርቱ፤ የታዩ ጠንካራ ጎኖችና ክፍተቶች የተመላከቱ ሲሆን፣ በቀጣይ ትኩረት ተደርገው በሚሰሩ ተግባራት ላይም የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች አቅጣጫ አስቀምጠዋል::









# ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ትውልድን በሥነምግባር እና በአካል የመገንባት ሀገራዊ ኃላፊነት አለበት - ክብርት ሸዊት ሻንካ







የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎችና ከፍተኛ አመራሮች በሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከል ዙሪያ ግንዛቤ እንዲጨብጡ የሚያግዝ ስልጠና ተሰጥቷል:: ይህ መድረክ ተቋማዊ ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን ለማስፈን ያለመ መሆኑ ተገልጿል::

የመድረኩን መክፈቻ ንግግር ያደረጉት የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ክብርት ሸዊት ሻንካ እንደገለጹት፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ትውልድን በአካልም በአእምሮም የመገንባት ትልቅ አገራዊ ኃላፊነት ያለበት ተቋም ነው:: ዘርፉ ሰፊ ከመሆኑ አንጻር ከተባባሪ ተቋማት አንዱ ከሆነው ከፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል በቅንጅት እየተሰራ እንደሚገኝ አስታውቀዋል:: የሙስና እና የብልሹ አሰራር ክፍተቶችን በመለየት ተጠያቂነትንና የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ በትኩረት እየተሰራ መሆኑንና አሁን እየተሰጠ የሚገኘው ስልጠናም የአመራሩን አቅም ለማሳደግ መሆኑን አብራርተዋል::

በመድረኩ ላይ የተገኙት የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው፤ ስልጠናው «የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት፤ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ!» በሚል መሪ ቃል የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል:: በሂደቱም ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ፣ የጥቅም ግጭት እና ሙስና መከላከል በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ስልጠናው እንደተሰጠ አስታውቀዋል:: ምክትል ኮሚሽነር አክለውም፣ የባህልና ስፖርት ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት ሰፊ በመሆኑ የመንግሥትን ከፍተኛ ትኩረት እንደሚጠይቅ አሳስበዋል::

አመራሩ የኮሪደር ልማት ስራን በትኩረት፣ በስኬት እንደሰራው ሁሉ፣ በማለቅ ላይ የሚገኘውን የአደይ አበባ ስታዲየም ቀሪ ስራዎች በትኩረትና በፍጥነት ሊያጠናቅቅ እንደሚገባ ተናግረዋል:: ከስፖርተኞች ምልመላና ቅጥር ጋር ተያይዘው የነበሩ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታትም አመርቂ ውጤት ለማምጣት በይበልጥ መስራት እንደሚገባ አመልክተዋል::

ስልጠናውን የሰጡት አሰልጣኝ ዶ/ር የሱፍ ኢብራሄም በበኩላቸው፤ ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሲጓደል የሀገርና የህዝብ ሀብት በከንቱ እንዲባክን እንደሚያደርግ አስገንዝበዋል:: «የጥቅም ግጭትን ተከላከልን ማለት ለሙስና በር ዘጋን ማለት ነው» ያሉት አሰልጣኙ፣ ሙስናን መዋጋት ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ ሲፈጠር ብልሹ አሰራርን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት እንደሚቻል አብራርተዋል:: በስልጠናው መድረክ ላይ ከተሳታፊዎች በርካታ ሃሳቦች የተነሱ ሲሆን፣ የሥነምግባር ትምህርትን አሁን ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ እየተሰጠ መሆኑ በጥሩ ጎኑ ተነስቷል:: አጣብቂኝ ሁኔታዎች ሲገጥሙ መወሰን የሚቻለው ህግን መሰረት በማድረግ ብቻ መሆን እንዳለበት አብራርተዋል:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) «መደመር» መጽሃፋቸው ላይ ስልጣን ያላቸውን ሙሰኞች «ባለከራባት ተምነሽናሽ ሌቦች» እንዳሏቸው በማስታወስ የፀረ-ሙስና ትግሉ የአመራሩን የላቀ ቁርጠኝነት የሚጠይቅ መሆኑ ተገልጿል::

## ሙስናን ለማጥፋት...ከገጽ 1 የዞረ

ሙስናን ለማጥፋት...ከገጽ 1 የዞረ

በመላምት ከሆነ የምንወስነው የሚሰራውንና የሚሰርቀውን ቀላቅለን እናጠፋለን፤ የሚጨበጥ መረጃ ካላችሁ ሳኩልንና ርምጃ ካልወሰድን እኛን ጠይቁን:: ሌብነት ጠቃሚ አይደለም፤ ማስረጃ ማግኘት በህግም በአስተዳደርም ርምጃ ለመውሰድ ያግዛል:: ሌብነት ክፉ መሆኑን አምነን መጀመሪያ ራስን መታገል አልፎ ሲሄድ ደግሞ በህግ የሚያስጠይቅ ማስረጃ መያዝ ጠቃሚ ይሆናል:: በዚህ አካሄድ የቀረው በጀት የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ መትጋት የምንችል ይመስለኛል ብለዋል::

የኢትዮጵያ ህዝብ በ7ኛው ሀገራዊ ጠቅላላ ምርጫ ለመንግሥት የሰጠው ድጋፍ ለዕቅዶች ስኬት እና ለሥርዓታዊ ሌብነት መጥፋት ያለውን ተስፋ እንደሚያመላክት ተናግረዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረጠን የተጀመሩ የኢኮኖሚና የፀረ-ሙስና ጥረቶችን በማጠናከር፣ የአገልግሎት አሰጣጥን አሻሽለን ለቀጣዩ ትውልድ የበለጸገች ሀገር እንድናስረክብ የጣለብንን አደራ ለመወጣት ነው ሲሉም አጽንኦት ሰጥተዋል::

በዚህም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማሻሻል፣ ሌብነትንና ሙስናን ለማጥፋት እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን የሚደረጉ ጥረቶች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አስገንዝበዋል:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለምንም ፍርሃት






በነጻነትና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ድምፁን ሰጥቷል ብለው፤ ይህም በታማኝነትና ሕዝብን በክብር ማገልገል ምን ያህል ፍሬያማ እንደሆነ በተግባር ያሳየ ነው ሲሉ አመልክተዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አክለውም፤ ባለፉት አመታት ተማሪዎች በራሳቸው ተማምነው ፈተና የሚወስዱበት አሰራር መተግበሩን ጠቅሰው፤ የኩራጃ ባህልን ማስረቀት እየተቻለ መሆኑን ገልጸዋል:: የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ፣ ኩረጃን ለማስቀረት፣ ትምህርትን በቴክኖሎጂ ለማስፋፋት እየተደረገ ያለው ሙከራ ተስፋ ሰጪ ነውም ብለዋል::

# አስራ አንድ ማዕከላትን እውን በማድረግ ቃላችንን በተግባር አሳይተናል - ከንቲባ አዳነች አቤቤ





ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎትን በሁሉም ክፍለ ከተሞች 11 (አስራ አንድ) ማዕከላትን እውን በማድረግ ቃላችንን በተግባር አሳይተናል ሲሉ ገለጹ:: ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸዉ ባሰፈሩት መልእክት ውድ የከተማችን ነዋሪዎች ፈጣን፣ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ግልፅ፣ ከአድሎና ጉቦ የፀዳ ፍትሃዊ አገልግሎት በሁሉም አካባቢ ማግኘት የሚያስችላችሁን ማዕከላት በማግኘታችሁ እንኳን ደስ

አላችሁ! ብለዋል::

ወደ ገጽ 4 የዞረ

# ለጉምሩክ ኮሚሽን ሠራተኞች በጥቅም ግጭት መከላከል ላይ ስልጠና ተሰጠ





በጉምሩክ ኮሚሽን የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት አመራሮች እና ባለሙያዎች "የጥቅም ግጭትን መለየትና ሙስናን መከላከል" በሚል ርዕስ ሥልጠና ተሰጥቷል።

በመድረኩ የተገኙት የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አቶ ተፈሪ መኮንን እንደገለጹት፤ የስልጠናው ዋና ዓላማ የሥነ-ምግባር ግንዛቤን ማሳደግ፣ ሥነ-ምግባራዊ የውሳኔ አሰጣጥን ማዳበር እንዲሁም በስራ ቦታ የሚፈጠሩ የጥቅም ግጭቶችን ቀድሞ መለየትና መከላከል ነው። አያይዘውም የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ አመራሮች እና ባለሙያዎች ደንበኞችን በቅንነት ማገልገልና የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት እንዳለባቸው አሳስበዋል። አቶ ተፈሪ አክለውም ለህግ የበለጠ ተገዥ የሆኑ እንዲሁም ከሙስና የጸዱ አመራሮችና ባለሙያዎችን ለማፍራት አበክሮ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በተመሳሳይ በጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የአሶሳ መቅረጫ ጣቢያ የሥራ ሂደት አስተባባሪ አቶ ሙስጠፋ አዜን ሥልጠናው ላይ በመገኘት መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን፣ ይህ መድረክ የቅ/ጽ/ቤቱን የሥራ ባህልና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር እና የአገልግሎት አሰጣጡ ከጥቅም ግጭትና ሙስና የጸዳ ሆኖ ተቋማዊ አገልግሎት ለመስጠት ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን በመጥቀስ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና እነዚህን ችግሮች መከላከል እንደሚገባ አሳስበዋል። በሥልጠናውንም የሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድንን ጨምሮ፣ ለሁሉም ሠራተኞች በቅርጫፍ ጣቢያ ደረጃ አገልግሎት አሰጣጥን ሥነ-ምግባራዊ በማድረግ የጥቅም ግጭትንና ሙስናን መከላከል የሚያስችል የግንዛቤ መፍጠሪያ ሥልጠና ተሰጥቷል።

# ለትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች በሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ስልጠና ተሰጠ

የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ከፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና ለተጠሪ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች ስልጠና ተሰጥቷል። ስልጠናው «የሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭትን መከላከል» በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሲሆን፣ በተቋማት ውስጥ ሥነምግባራዊ ውሳኔዎችን ለመወሰንና ሙስናን ለመከላከል ያለመ መሆኑ ተገልጿል።

በመድረኩ የተገኙት በኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታና ፀረ-ሙስና ስልጠና ባለሙያ ወ/ሮ ሜሮን ዳምጤ እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ «የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት፤ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ!» በሚል መሪ ቃል በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ውስጥ ተከታታይ ስልጠናዎችን እየሰጠ ይገኛል። የዛሬው መድረክም ይህንን ሀገራዊ ስልጠና ይበልጥ ለማጠናከር የተዘጋጀ የስልጠናው አንዱ አካል መሆኑን አብራርተዋል።

ስልጠናውን የሰጡት ዶ/ር ዘውዴ ዛኬ በበኩላቸው፣ ሥነምግባር በጽንሰ-ሀሳብ ደረጃ ብቻ የሚቀመጥ ሳይሆን በተግባር መሬት ሊወርድ የሚገባው እሴት መሆኑን አፅንኦት ሰጥተዋል። አሰልጣኙ አክለውም "ሥነምግባርን ተላብሰን የምንሰራ ከሆነ ጤናማ የስራ አካባቢን መፍጠር፤ ለሌሎችም አርዓያ መሆን ይቻላል" ያሉ ሲሆን፣ የሥነምግባር መርሆዎች ለሙያዊ ስራ ስኬታማነት ብቻ ሳይሆን ለጤናማ ማህበራዊ መስተጋብርም መሰረት መሆናቸውን አስገንዝበዋል።





ይህ በሁለቱ ተቋማት ትብብር የተሰጠው ስልጠና በአመራሩ ዘንድ ያለውን የውሳኔ አሰጣጥ ጥራት ለማሳደግ፣ የጥቅም ግጭቶችን በቅድሚያ ለመከላከል እና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ግልጽነትን ለማስፈን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል።

## አስራአንድ ማዕከላት… ከገጽ 3 የዞረ

በአቃቂ ቃሊቲ እና በለሚ ኩራ ክፍለ ከተሞች ሁለት አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ከፍተን በከተማችን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በአስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች ማዕከላትን እውን አድርገናል። በእነዚህ ማዕከላት ለህብረተሰቡ 50 በመቶ ያህል የመንግስት አገልግሎቶች እጅግ ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እየተሰጠ ይገኛል። ቀጣዩ ስራችን ደግሞ ቀሪዎቹን 50 በመቶ አገልግሎቶች ወደ እነዚህ ማዕከላት እንዲገቡ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጥን ሙሉ በሙሉ በማዘመን ለነዋሪዎቻችን እርካታና እፎይታን መፍጠር ይሆናል ብለዋል።

ለረጅም ዘመን የተተበተበ ቢሮክራሲ፣ በብልሹ አሰራር ውስጥ የነበረውንና ለመለወጥ ጥረቶች ቢደረጉም ባለመለወጡ የሪፎርም ዝለትና ሊለወጥ አይችልም ወደሚል ተስፋ መቁረጥ ደረጃ ላይ የደረሰውን የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ተግተን በመስራት ትልቅ ሽግግር ያደረግንበት፣ ህዝባችን ጊዜውንና ገንዘቡን ለልማት እንዲያውል በሚያደርግ ማዕከል መተካት ችለናል ሲሉ ገልጸዋል።

በሀገራችን ሙያተኞች የገነባናቸው እነዚህ ተቋማት የሀገራዊ ህልሞቻችን በለውጥ መገስገስ እንደምንችል ማረጋገጫዎች ናቸው። የዛሬዎቹን ጨምሮ በአጭር ጊዜ በጥራት በመገንባት፣ በማማከር እንዲሁም ተቋሞቹን በቴክኖሎጂ እንዲሟሉ የበኩላችሁን አስተዋፅኦ ላደረጋችሁ ሁሉ በከተማችን ነዋሪዎች፣ በከተማ አስተዳደሩና በራሴ ስም ከልብ አመሰግናለሁ ሲሉ ከንቲባ አዳነች አቤቤ መልእክት አስተላልፈዋል።

# ህብረተሰቡ የሚያስተውላቸውን ብልሹ አሰራሮች እንዲጠቁም ጥሪ ቀረበ




በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ለከተማዋ ፈጣን እድገትና ለነዋሪዎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ወሳኝ ሚና ካላቸው ተቋማት አንዱና ዋነኛው ነው:: ይሁን እንጂ ቢሮው ተቋማዊ አሰራሩን ካለማዘመኑ ጋር ተያይዞ አገልግሎት አሰጣጡ የተንዛዛና ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ ሆኖ ቆይቷል::

ቢሮው ይህን ችግር ከመሰረቱ ለመቅረፍና አሰራሩን ለማዘመን በ2016 በጀት ዓመት ተቋማዊ ሪፎርም አድርጓል:: ዛሬ ላይም ይህን የሪፎርም ስራ ወደ ላቀ ምዕራፍ ለማሸጋገር በተያዘው በጀት ዓመት ምዕራፍ አንድ የሲስተም ማሻሻያ በማድረግ ተገልጋዩ በተግባር ያረጋገጠለትን ውጤት ማምጣት ችሏል:: በቀጣይም ጊዜውን የዋጀ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ተገልጋዩን ለመካስና እርካታውን ለማሳደግ በሁለተኛው ምዕራፍ ሙሉ ለሙሉ የተቋሙን አገልግሎት በቴክኖሎጂ ለማስደገፍ የሚያስችለውን ስራ የመጨረሻ ደረጃ ላይ ስለማድረሱም ተገልጿል::


እያንዳንዱ ተቋማዊ ተግባር ለሕዝብ እንደመሆኑ የሕዝቡን ተሳትፎና ድጋፍ ይሻል የሚለው የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣ በቢሮው ከማዕከል እስከ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የሚገጥሙትን ወይም የሚያስተውሏቸውን እንግልቶችና ብልሹ አሰራሮች በማስረጃ በማስደገፍ ዘወትር በስራ ሰዓት በ7079 ነፃ የስልክ መስመር ጥቆማ በመስጠት የበኩላቸውን የዜግነት ሚና እንዲወጡ ዳግም ጥሪ አቅርቧል::

# በጋምቤላ ክልል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሕግ የበላይነት ማስከበር ስራ ተጠናክሮ መቀጠሉን ገለጸ

የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የሥነ-ምግባር መኮንን ጋር በቅንጅት ባደረጉት ጥብቅ ክትትልና ለክልሉ ፍትህ ቢሮ የሙስና ምርመራ ክፍል ባስተላለፋት ጥቆማ መሠረት፣ የመንግስትን የግዥ አሰራር መመሪያ በመጣስ የሙስና ወንጀል በፈጸሙ ግለሰቦች ላይ ይፋዊ የክስ ሂደት ተመሠረተ:: ተከሳሾች የክልሉ ፕላን ቢሮ የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት ቡድን መሪ እና የአንድ የግል ተቋም ባለቤት፣ በአሁኑ ወቅት ጉዳዩ በፍርድ ቤት በሂደት ላይ ይገኛል::

የተፈጸሙት ዋና ዋና የሕግ ጥሰቶችና የሙስና ወንጀሎች ያለ ግልጽ ጨረታ ግዥ መፈጸም አንደኛ ተጠርጣሪ የመንግስትን መመሪያ በመጣስ ያለ ምንም ግልጽ ጨረታ እቃዎች ገዝተው በማቅረብ 1,458,450.50 ብር ከመንግስት ካዝና እንዲወጣ ማድረጋቸው፤ ያልተሰራን ስራ እንደተሰራ ማስመስከር በዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተተን ስራ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ በመተግበር 1,200,000.00 ብር ያለአግባብ ወደ ግል የባንክ አካውንት እንዲገባ መደረጉ፤ በሕገ-ወጥ ስራ መተባበር ሁለተኛ ተጠርጣሪ በጨረታ ያልተለየ ሕገ-ወጥ የሥራ ውል በመፈራረም እንዲሁም የድርጅታቸውን የቪኤቲ (VAT) ሽያጭ ሰነድ አሳልፈው በመስጠት ተባባሪ ሆነው በመገኘታቸው መሆኑ ተናግረዋል::

የጋምቤላ ክልል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የመንግስትን ሃብት ለመታደግ የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ተገልጿል:: ማንኛውም የክልሉ የመንግስት መስሪያ ቤትና የልማት ድርጅት የፋይናንስና የግዥ ስራዎችን በሕጉ መሠረት ብቻ እንዲፈጽሙ እያሳሰበ፤ የተቋማት



የሥነ-ምግባር መኮንኖች ለተቋማቸው ተጠያቂነት መስፈንና ለቅድመ-መከላከል ስራው ከፍተኛ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪውን አቅርቧል::

# ርዕሰ -አንቀፅ

## በሪፎርም ውስጥ ምቹ የሥራ አካባቢ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለው በጎ አስተዋጽኦ!

በመንግሥት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም አውድ ውስጥ ”ምቹ የሥራ አካባቢ” ማለት ሠራተኞች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በላቀ ብቃት፣ በደህንነት ስሜት፣ በቅንነት እና በከፍተኛ መነሳሳት እንዲወጡ የሚያስችል አካላዊ፣ ድርጅታዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ምህዳር ነው። የዚህ ምቹ የሥራ አካባቢ ዋነኛ መገለጫዎች፦ ተስማሚና ሳቢ የሥራ ቦታ፣ ዘመናዊ የሥራ መሣሪያና ቴክኖሎጂ፣ ግልጽነት የሰፈነበት አመራርና ተጠያቂነት፣ የሠራተኞች ክብርና ተሳትፎ መጎልበት፣ ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ እንዲሁም በሥራ መነሳሳት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ናቸው።

በሪፎርም አውድ ውስጥ ምቹ የሥራ አካባቢን የመፍጠር ዋና ዓላማ የመንግሥት ተቋማትን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽ እና ለዜጎች ተጠያቂ ማድረግ ነው። ይህ ዓይነቱ ምቹ ሁኔታ የአገልግሎት ጥራትን በከፍተኛ ደረጃ ያሻሽላል፣ የሠራተኞችን የመፈጸም ቅልጥፍና ያሳድጋል፣ የተቋማትንም አጠቃላይ አፈጻጸም በጽኑ መሠረት ላይ ያጠናክራል።

ይህንን ታላቅ ዓላማ በተግባር ለመተርጎም በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተጀመረው ስር ነቀል ሪፎርም እና ምቹ የሥራ አካባቢን የመፍጠር ንቅናቄ በአሁኑ ወቅት በስፋት እየተገበረ ይገኛል። የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንም በቅርብ ዓመታት ውስጥ ምቹ የሥራ አካባቢን የሚፈጥሩ ተቋማዊ ለውጦችንና የአሠራር ማዘመን ሥራዎችን በውጤታማነት ሲያከናውን የቆየ ሲሆን፣ አሁንም ይበልጥ አጠናክሮ ቀጥሎበታል። ኮሚሽኑ የሰው ኃይሉን በማብቃት፣ የአሠራር ለውጥ በማምጣት እና የቴክኖሎጂ ትጥቅ በመታጠቅ ተቋሙን በልበ ሙሉነት ወደፊት እያስወነጨፈው ይገኛል። ለዚህ ስኬት ደግሞ የተቋሙ አመራር ያሳየው ቁርጠኝነት ጉልህና የማይተካ ሚና ነበረው።

በቴክኖሎጂ ረገድ፣ ሀገራችን በ2030 ሙሉ በሙሉ ዲጂታል የመሆን ብሔራዊ ግንባታ ራዕይን መሠረት በማድረግ፣ የኢትዮጵያ ዲጂታል የሀብት ምዝገባ ሥርዓት (EARS) እና ብሔራዊ የሙስና መጠቆሚያ ሥርዓት (NCRS) ተቀርጾ ወደ ሙሉ ሥራ ከገባ ሰነባብቷል። ኮሚሽኑ እነዚህን ዘመናዊ ሥርዓቶች በአግባቡ በመጠቀም በሙስና መከላከልና መረጃ በማመንጨት ረገድ ተጨባጭና አስደናቂ ውጤቶችን እያስመዘገበ ይገኛል። የኮሚሽኑ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እንደ ግንባር ቀደም ማሳያ የሚነሳ እንጂ፣ በአገር አቀፍ ደረጃም የአገልግሎት አሰጣጥን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያቀላጥፉ እና በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ፒኤችዲ) አነሳሽነትና መሪነት የተገነቡት የ”መሶብ” የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫዎች በተጨባጭ ተገንብተው ለአገልግሎት በቅተዋል፣ እየተገነቡም ይገኛሉ። እነዚህ ማዕከላት ከሥራ አካባቢ ምቾት አንጻር ሲፈተሹ፣ ለአገልጋዩ ሠራተኛም ሆነ ለተገልጋዩ ዜጋ ፍጹም ምቹና ሳቢ በሆነ ሁኔታ ላይ የተመሠረቱ የለውጥ ማሳያዎች ናቸው።

በአጠቃላይ፣ ምቹ የሥራ አካባቢ የተገልጋዩን ዘላቂ ፍላጎትና የአገልግሎት ቅልጥፍና የሚያሟላ፣ በአንጻሩ ደግሞ የአገልግሎት ሰጪውን ምቾት፣ ደህንነትና ክብር ማዕከል ያደረገ በመሆኑ፤ ሁሉም የመንግሥት ተቋማት ይህንን ምቹ የሥራ ሁኔታ በፍጥነት ተግባራዊ ሊያደርጉና ተደራሽ ሊሆኑ እንደሚገባ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አጥብቆ ያሳስባል።


የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993
ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ጋዜጣ



ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission


**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች EARS**

**ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች**


ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1


NCRS

# ሳይቃጠል በቅጠል

## የሲቪል ማህበራት ሙስናን ለመዋጋት እና መልካም አስተዳደርን ለመገንባት ያላቸው ሚና

ሙስናን መዋጋት እና የመልካም አስተዳደር እሴቶችን መገንባት የአንድ ወገን ወይም የመንግስት ብቻ ኃላፊነት አይደለም:: ሙስና ተቋማትን የሚያዳክም፣ ፍትህን የሚያዛባ እና የሀገርን የኢኮኖሚ እድገት የኋሊት የሚጎትት ነቀርሳ በመሆኑ፣ እሱን ለመዋጋት የሲቪል ማህበራት ሚና ምትክ የሌለው የዲሞክራሲ ምሰሶ ነው:: ሲቪል ማህበራት በመንግስት እና በህዝብ መካከል እንደ ድልድይ በመሆን፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የሚያደርጉ፣ የህዝብ ድምፅ እና የፍትህ ጠባቂ "ነጻ አይኖች" ናቸው:: በዚህም የሚከተሉት ሚና ይኖራቸዋል::

**የግንዛቤ ማስጨበጥ፣ የሥነ-ምግባር ግንባታ እና የህዝብ ንቅናቄ ስራዎች:**
- የሲቪል ማህበራት ዋነኛ እና የመጀመሪያው መሳሪያ ህብረተሰብን ማስተማር፣ ማንቃት እና በባለቤትነት ስሜት ማነሳሳት ነው:: ሙስና በአገርና በትውልድ ላይ የሚያመጣውን መጥፎ አደጋ ለህብረተሰቡ በማስረዳት ረገድ ቀዳሚውን ድርሻ ይወስዳሉ:: የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዜጎች መብትና ግዴታቸውን እንዲረዱ፣ ሙስና መብትን የሚጋፋ ወንጀል መሆኑን እንዲገነዘቡ እና እምቢ ለሙስና ማለት እንዲችሉ ሰፊ የንቅናቄ ስራዎችን ይሰራሉ::

በአንዳንድ ማህበረሰቦች ዘንድ ሙስናን ወይም ጥቅማጥቅም መስጠትን እንደ ተራ ነገር ወይም እንደ አቋራጭ መንገድ የመውሰድ የተሳሳተ አመለካከት አለ:: ሲቪል ማህበራት ይህንን ባህል በመቀየር፣ ሙስና ማህበራዊ ነውር እና የሀገር ሌባ መሆኑን የሚያሳዩ የስነ-ጥበብ፣ የሚዲያ እና የውይይት መድረኮችን በመጠቀም ግንዛቤ ይፈጥራሉ::

**የፀረ-ሙስና እሴቶችን ማስረጽና ስልጠናዎችን መስጠት:-** ለወጣቶች፣ ለሴቶች፣ ለሀይማኖት መሪዎች እና ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ታማኝነትን፣ ፍትሃዊነትን እና ተጠያቂነትን የሚያስተምሩ ስልጠናዎችን ያዘጋጃሉ:: ይህም ነገ አገር የሚረከብ ስነ-ምግባር ያለው ትውልድ ለመቅረጽ ይረዳል::

**የጥቆማ እና የክትትል ሚና:-** የሲቪል ማህበራት የመንግስትን አሰራር፣ የበጀት አጠቃቀምን እና የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥን በቅርብ በመከታተል የሙስና ስጋቶችን ቀድመው የሚያጋልጡና የህዝብ ንብረትን የሚጠብቁ ጠባቂዎች ናቸው:: ለህዝብ ልማት (ለምሳሌ ለትምህርት ቤቶች፣ ለጤና ጣቢያዎች፣ ለእርዳታ) የተመደበ ገንዘብ በትክክል ለታለመለት አላማ መዋሉንና አለመዋሉን፣ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ከመሬት ወርደው ይከታተላሉ:: ከፍተኛ የሙስና ስጋት ያለባቸውን የመንግስት የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች እንዲሁም የሰራተኛ ቅጥር እና እድገት አሰራሮችን በቅርብ ያጠናሉ፤ ህገ-ወጥ አሰራርና የአድልዎ ድርጊቶች ሲኖሩም ለህዝብና ለሚመለከተው አካል ያጋልጣሉ:: በመሆኑም የመንግስት መረጃዎች፣ ውሳኔዎችና ፖሊሲዎች ለህዝብ ግልጽ እንዲሆኑ እና ጋዜጠኞች፣ ተመራማሪዎችና ዜጎች መረጃን በቀላሉ እንዲያገኙ ግፊት ያደርጋሉ::

**የተስተካከለ አሰራር፣ የህግ እና የፖሊሲ ማሻሻያ ጥበቃ:-** የሲቪል ማህበራት ችግሮችን ከመጠቆም እና ከመጮህ ባለፈ፣ ሙስናን በዘላቂነት የሚከላከሉ ጠንካራ ህጎች እና መዋቅሮች እንዲዘረጉ ተፅዕኖ ፈጣሪ ስራዎችን ይሰራሉ:: የህግ ማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ: ክፍተት ያለባቸውን ወይም ለሙስና በር የሚከፍቱ የፀረ-ሙስና ህጎችን፣ የአሰራር ደንቦችን በጥናትና ምርምር በመለየት፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ያካተቱ የፖሊሲ ማሻሻያ የውሳኔ ሃሳቦችን ለመንግስት እና ለህግ አውጪ አካላት ያቀርባሉ:: እንዲሁም ሙስናን የጠቆሙ ወይም የመሰከሩ ግለሰቦች ከስራ መባረር፣ ከአካል እና ከህይወት አደጋ የሚጠበቁበት ጠንካራ የህግ ከለላ እንዲኖር ይሟገታሉ:: ይህ ካልሆነ ዜጎች ሙስናን ለመጠቆም ስለሚፈሩ የማህበራቱ ጥበቃና ሙግት ወሳኝ ነው:: የተቋማትን ነጻነት መደገፍ: እንደ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ የኦዲት መስሪያ ቤቶች እና የፍትህ አካላት ከመንግስት የፖለቲካ ጣልቃገብነት ነጻ ሆነው እንዲሰሩ እና በቂ በጀት እንዲመደብላቸው ግፊት ያደርጋሉ::

**ለተጎጂዎች ድምፅ መሆንና ነጻ የህግ ድጋፍ መስጠት:**
- ብዙውን ጊዜ በሙስና እና በመጥፎ አስተዳደር ምክንያት መብታቸው የሚገፈፈው፣ መሬታቸው የሚቀማው ወይም አገልግሎት የሚከለከሉት አቅም የሌላቸው፣ ድሆች እና ድምፅ አልባ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው:: በሙስና ምክንያት በደል ለደረሰባቸው፣ መብታቸውን ማስከበር ላልቻሉ ዜጎች ነጻ የህግ ምክር ይሰጣሉ፤ አልፎ ተርፎም ፍርድ ቤት ድረስ በመሄድ በነጻ ጠበቃ ቆመው ይከራከራሉ:: ሰፊ የህዝብ ጥቅም የሚነኩ የሙስና ጉዳዮችን (ለምሳሌ የአካባቢ ብክለት፣ የህዝብ መሬት ዘረፋ) ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ መንግስት ወይም የግል ኩባንያዎች ማስተካከያ እንዲያደርጉ ያስገድዳሉ:: የፍትህ መጓተትን መታገል: "የዘገየ ፍትህ እንደተከለከለ ፍትህ ይቆጠራል" እንደሚባለው፣ የሙስና መዝገቦች በፍትህ አካላት ዘንድ ሳይጓተቱ፣ ፈጣን እና ገለልተኛ ውሳኔ እንዲያገኙ የማያቋርጥ ክትትልና ግፊት ያደርጋሉ::

በአጠቃላይ፣ መንግስት የቱንም ያህል ፍላጎት ቢኖረው ብቻውን ሙስናን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት አይችልም:: የሲቪል ማህበራት በነጻነት፣ በገለልተኝነት እና በደህንነት መንቀሳቀስ ሲችሉ ብቻ ነው የመንግስትን ተጠያቂነት ማረጋገጥ እና ህዝቡን የመብቱ ባለቤት ማድረግ የሚቻለው:: ማህበራቱ "የዲሞክራሲ እና የፍትህ ጠባቂ" ናቸው:: ነገር ግን፣ ከዚህ በበለጠ ውጤታማ ለመሆን የሲቪል ማህበራት በውስጥ አሰራራቸው ግልጽነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ለሌላው አርአያ መሆን አለባቸው:: ከመንግስት ጋር የገንቢ ትብብር እና የባለሙያ ድጋፍ ግንኙነትን ማጠናከር ይኖርባቸዋል፣ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ማለትም የፌዴራል የስነምግባር እና የፀረሙስና ብሔራዊ የጥቆማ ስርዓት(NCRS) ወደ ኮሚሽኑ መምጣት ሳይገባቸው በስልክ ወይም በኮምፒውተር ያሉበት ሆነው የጥቆማን ስርዓት መጠቀም፣ ማስተዋወቅ እና የህዝብ ተሳትፎን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል:: የሲቪል ማህበራት ሚና ሲጎለብት፣ የመልካም አስተዳደር እሴቶች ይገነባሉ፤ ሀገራችንም በታማኝነት እና በእኩልነት ላይ ወደተመሰረተ ዘላቂ ብልጽግና እየተጓዘች ያለችውን ጉዞ በአጭር ጊዜ እውን ታደርጋለች::

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

## የፓርላማ አባሏ ቤት ውስጥ ከፍተኛ ወርቅ በተጨማሪ ከወርቅ የተሰራ የውስጥ ሱሪ መገኘቱ ተገለጸ

በኢራቅ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አሊ አል-ዛይዲ (Ali al-Zaidi) መሪነት በሀገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ የፓርላማ አባላትና ነጋዴዎች ላይ ያነጣጠረ እጅግ ሰፊ እና ከባድ የፀረ-ሙስና ዘመቻ እየተካሄደ ይገኛል።



በቁጥጥር ስር በዋሉት የፓርላማ አባላት መኖሪያ ቤቶች ላይ በተደረገው ድንገተኛ ፍተሻ በሚሊዮን የሚቆጠር የዶላር እና የዲናር ጥሬ ገንዘብ፣ በርካታ ኪሎ ግራም ንጹህ ወርቅ፣ የተቀበሩ የገንዘብ ሳጥኖች፣ የቅንጦት መኪናዎች እና የፈረስ እርባታ ሳይቀር መገኘቱ ተረጋግጧል። በተለይም በዚች የፓርላማ አባል ሂንድ አል አባሲ ቤት ውስጥ ከተገኘው ከፍተኛ ወርቅ በተጨማሪ "ከወርቅ የተሰራ የውስጥ ሱሪ" መገኘቱ በማህበራዊ ሚዲያ እና በዜና አውታሮች ላይ ከፍተኛ መነጋገሪያ ሆኗል። ሂንድ አል አባሲ (Hind al-Abbasi) የተባሉት የኢራቅ የፓርላማ አባል በዚሁ የሙስና እና የህዝብ ገንዘብ ማጭበርበር ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር መዋላቸው በመገናኛ ብዙሀን እየተገለጸ ነው። በኢራቅ መንግስት እና የስነ-ምግባር ኮሚሽን በወጣው ይፋዊ ትዕዛዝ መሰረት፣ በኩርዲስታን ክልል ተሸሽገው ሳለ በቁጥጥር ስር ውለው ለባግዳድ የደህንነት አካላት ተላልፈው ተሰጥተዋል።

ይህ ፍተሻ የተደረገው በአንድ ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን፣ እስካሁን ከ40 በላይ የፓርላማ አባላት እና ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ያለመከሰስ መብት ተነስቶባቸው በቁጥጥር ስር የዋሉበት ትልቅ አገራዊ ዘመቻ አካል ነው። በአጠቃላይ በቁጥጥር ስር ከዋሉት ባለስልጣናት መኖሪያ ቤቶች ውስጥ እስካሁን ከ130 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት የጥሬ ገንዘብ እና የወርቅ ክምችት በመርማሪዎች መያዙ ተገልጽዋል። ከዚህ ዜና ጋር ተያይዞ የህግ አውጭ አካላት ህዝብን ወክለው ህግ የመቅረጽ፣ የመንግስትን አሰራር የመቆጣጠር እና የሀገርን ሀብት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ታላቅ አደራ ያለባቸው ተቋማት ቢሆኑም፣ እነዚህ አካላት ራሳቸው በሙስና ሲዘፈቁ ግን የሚያሳዩት የቅንጦት ልክ ማጣት እና በሀገር ላይ የሚያመጡት ጉዳት እጅግ የከፋ ይሆናል።

ሙስና በባህሪው የማይረካ ስግብግብነትን የሚወልድ በመሆኑ፣ የፓርላማ አባላት ያላቸውን ህጋዊ ያለመከሰስ መብት እንደ ከለላ በመጠቀም "ማንም አይነካኝም" በሚል የልብ ሙሉነት ፍርሃት ይርቃቸዋል። የስልጣን ዘመናቸው የተገደበ መሆኑን ስለሚያውቁም "ስልጣን ላይ እያለሁ ማጋበስ አለብኝ" በሚል የችኮላ ስነ-ልቦና በመነዳት፣ ያገኙትን የህዝብ ገንዘብ ያለምንም መቆጠብ ለታላላቅ ቪላ ቤቶች፣ ለውድ መኪናዎች እና ለተለያዩ ከልክ ያለፉ የቅንጦት ዕቃዎች ማከማቻነት ያውሉታል። ይህ ከህግ በላይ የመሆን የበላይነት ስሜት እርስ በርስ እስከ መፎካከር የሚያደርስ የስነ-ልቦና መዛባትንና የቅንጦት አባዜን በውስጣቸው ይፈጥራል።

የዚህ አይነቱ ስግብግብነት በሀገር ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ደግሞ የትኛውንም የመንግስት መዋቅር ከሚገጥመው ውድቀት በላይ የከፋ ነው። የፓርላማ አባላት በሙስና ሲሻረኩ ህግ የሚያወጡት ለህዝብ ጥቅም ሳይሆን ለራሳቸው ወይም ጉቦ ለሚሰጧቸው አካላት መከላከያ የሚሆን በመሆኑ፣ ሙስናን የሚቀጡ ህጎችን ያላላሉ፤ በዚህም የህግ የበላይነት ይናዳል።

ከዚህም በላይ አስፈጻሚውን አካል የመቆጣጠር እና የበጀት አጠቃቀሙን የመመርመር ስልጣናቸው "እኔም በልቻለሁ፣ አንተም ብላ" በሚል ጥቅማ ጥቅም ስለሚታወር የመንግስት ቁጥጥር ስርአቱ ሙሉ በሙሉ ሽባ ይሆናል። ህዝብ ተስፋ አድርጎ የመረጣቸው አካላት በቅንጦት ሲንደላቀቁ እርሱ ግን መሰረታዊ ፍላጎቶችን አጥቶ ሲሰቃይ፣ በመንግስት ላይ ያለው እምነት ስለሚከስም ጉዳዩ ወደ ህዝባዊ አመጽ እና አለመረጋጋት ያመራል። በመጨረሻም ለልማትና ለድህነት ቅነሳ መዋል የነበረበት የሀገር በጀት በጥቂት ግለሰቦች ካዝና ውስጥ ታጉሮ ሲቀመጥ ወይም ወደ ውጭ ሀገር ሲሸሽ፣ የውጭ ኢንቨስተሮችም በሙስና ምክንያት መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ ስለሚሸሹ ሀገሪቱ ለማገገም በሚያስቸግር የኢኮኖሚ ውድቀትና የድህነት አዙሪት ውስጥ እንድትሰምጥ ያደርጋታል። የዚህ ማሳያ ደግሞ የኢራቅ የፓርላማ አባል ምስክር በመሆኗ የህግ አውጭ አካላት ከሙስና መራቅ አለባቸው።

# መልካም ዜጋ

## መልካም ዜጋ የነገዋ አገር ግንባታ መሰረት ነው!

አንድን አገር አገር የሚያሰኛትና ወደፊት የሚያስጉዛት ሰፊ መሬቷ ወይም የተፈጥሮ ሀብቷ ብቻ ሳይሆን፣ በውስጧ የሚኖረው ሕዝብ የሚያሳየው ስነ-ምግባርና አገራዊ ፍቅር ጭምር ነው። በተለይም በዚህ ዘመን ለአገር ዕድገት፣ ሰላምና ብልጽግና 'መልካም ዜጋ' መሆን አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆኗል። ለመሆኑ መልካም ዜጋ ምንድን ነው? አንድን ግለሰብስ መልካም ዜጋ የሚያሰኙት ዋና ዋና እሴቶችና መገለጫዎች ምንድን ናቸው?

ስነ-ምግባር እና መልካም ዜግነት ሰው ሕይወቱን በክብር እና በስነ-ምግባር ማሳደግ ለአገር ግንባታ መሰረት ነው። ስነ-ምግባር ማለት ለራሱና ለሌሎች ክብር መስጠት፣ በቃልና በተግባር ግልጽነትን መጠበቅ እና በማኅበረሰብ ውስጥ በሰላም መኖር ማለት ነው። ስነ-ምግባር ከመልካም ዜግነት ጋር በተያያዘ ሲኖር ሕይወትን በተስፋ እና በእምነት ያሳድጋል። በማኅበረሰብ ውስጥ እንደ መብራት በመስራትም ሰውን ከጭቆና እና ከሙስና ያወጣል። መልካም ዜጋ ሲሆን ሰው ለሌሎች እንደ ምሳሌ ይቆማል፤ ሕግን ያከብራል፣ ማኅበራዊ ግዴታዎችን ይፈጽማል፣ ለሌሎችም በክብር ይናገራል።

መልካም ዜግነትና ስነ-ምግባር ከሙስና መከላከል ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። በዚህ አውድ ሙስና ማለት አድልዎ በማድረግ፣ መብትንና አሰራርን በማዛባት አግባብ ያልሆነ ጥቅምን መፈለግ ነው። ሙስና በማኅበረሰብ ውስጥ እምነትን ያፈርሳል፣ እርስ በርስ መተማመንን ያጠፋል፣ ሰውንም ከራሱ ክብር ያርቃል፣ ዝቅ ያደርጋል። መልካም ዜጋ ሲሆን ግን ሰው ሙስናን በቃልና በተግባር ይከላከላል፤ ሙስና ሲቀንስ የማኅበረሰቡ እምነት ይጠናከራል፣ ራሱንም በክብር ያስቀምጣል። ስለሆነም መልካም ዜግነት፣ ስነ-ምግባር እና ሙስና መከላከል በአንድነት ሲኖሩ ማኅበረሰብን በሰላም ያጠናክራሉ፣ ሕይወትንም በክብር ያሳድጋሉ።

አንድን ግለሰብ መልካም ዜጋ የሚያሰኙት ዋና ዋና ምሶሶዎች የሚከተሉት ናቸው።

**ሕግን ማክበር እና ታማኝነት፦** መልካም ዜግነት የሚጀምረው አገራዊ ሕጎችንና ሥርዓቶችን ጠንቅቆ በማወቅና በማክበር ነው። አንድ መልካም ዜጋ የራሱን መብት ከማስከበር ባለፈ የሌሎችን መብት ያከብራል፤ ሕግ ሲጣስና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ በዝምታ አይመለከትም። ከግል ጥቅም ይልቅ የጋራና የሕዝብ ጥቅምን በማስቀደም፣ ከሙስና እና ከአድልዎ የጸዳ የሕይወትና የሥራ መስመርን ይከተላል።

**የሥራ ስነ-ምግባር እና አገራዊ ኃላፊነት፦** ማንኛውም ዜጋ በተሰማራበት የሙያ መስክ ሥራውን በትጋት፣ በጥራትና በቅንነት ሲወጣ መልካም ዜግነቱን በተግባር እያሳየ ነው። ይህ ታማኝነት ግብርንና ታክስን በወቅቱ ከመክፈል ጀምሮ፣ በአገራዊ ምርጫዎች ላይ በንቃትና በኃላፊነት ስሜት እስከ መሳተፍ ድረስ ያለውን ሰፊ ማኅበራዊ ኃላፊነት ያካትታል።

**የአካባቢ ጥበቃ እና አብሮነት፦** መልካም ዜጋ የነገውን ትውልድ አሻራ ያስባል። ለዚህም ነው የተፈጥሮ ሀብትን በጥንቃቄ የሚያስተዳድር፣ አካባቢውን የሚንከባከብና አረንጓዴ አሻራውን የሚያኖር። ከተፈጥሮ ባሻገርም፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ልዩነቶችን (ብሔር፣ ሃይማኖትና አመለካከትን) አክብሮ፣ በሰላምና በውይይት አብሮ የመኖርን ባሕል ያዳብራል።

በጥቅሉ መልካም ዜግነት ከመብት ጥያቄ ባሻገር የኃላፊነት ድርሻን በቅንነት መወጣት ነው። እያንዳንዱ ሰው በቆመበት የሥራና የሕይወት መስክ የሚያሳየው ታማኝነት፣ ቅንነትና ሕግ አክባሪነት ተደምሮ የተሻለችና የበለጸገች አገርን ለመገንባት ዋናኛው መፍትሔ ነው። ስለሆነም የፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን "መልካም ስነ-ምግባርን በመገንባት እና ሙስናን በመከላከል መልካም ዜጋ እንሁን!" የሚል ወሳኝ መልዕክቱን ያስተላልፋል።

# ኪነ-ጥበብ

## ባለአረንጓዴ ዓይኑ ጭራቅ…

”አረንጓዴ ዓይን ያለው ጭራቅ” የሚለው ሐረግ፣ ከዊሊያም ሼክስፒር ታዋቂው የ”ኦቴሎ‘ ድራማ የተወሰደና ስለ ቅናት አስከፊነት የሚገልጽ ፍልስፍና ነው፡፡ አሁን ግን የዚህን ጭራቅ ዓይን ወደ ሙስና እይታ አምጥተን እንመለከተዋለን፡፡ በአንድ ወቅት፣ በታላላቅ ከተሞችና በሥልጣን መንገዶች መገናኛ ላይ የሚኖር፣ ስሙ የማይጠራ ግን ጥላው በሁሉም ቦታ የሚያርፍ አንድ ”አረንጓዴ ዓይን ያለው ጭራቅ‘ ነበረ ይባላል፡፡ ይህ ጭራቅ እንደ ሌሎቹ አስፈሪ ፍጥረታት ጫካ ውስጥ አይኖርም፤ ይልቁንም መኖሪያው በሰው ልጅ የልብ ስንጥቅና በምኞት መጋዘኖች ውስጥ ነው፡፡

ጭራቁ መጀመሪያ ሲመጣ እንደ ወዳጅ ነው፤ በጆሮህ ላይ ”ይገባሃል… ይህ ላንተ ቀላል ነው? እያለ በሹክሹክታ ይጀምራል፡፡ አረንጓዴ ዓይኖቹ እንደ ብርቅዬ ዕንቁ ያበራሉ፤ ያንተን ድካም ብቻ ሳይሆን የጎደለህን ሁሉ የሚሞሉ ይመስላሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ዓይኖች የሚያዩት ልማትን ሳይሆን መበስበስን ነው፤ የሚያዩት ግንባታን ሳይሆን ንቅዘትን ነው፡፡ ይህን ጭራቅ ልዩ የሚያደርገው አንድ ባሕርይ አለው፦ በበላ ቁጥር አይጠግብም፣ ይልቁንም ይራባል፡፡ የአንዱን ድሃ እንጀራ ሲቀማ፣ የሌላውን ሕመምተኛ መድኃኒት ሲሰርቅ፣ አልፎም የሀገርን ተስፋ ሲውጥ አረንጓዴ ዓይኖቹ በደስታ ይበራሉ፡፡ እርሱ በገባበት ቢሮ ግድግዳዎቹ ማውራት ያቆማሉ፣ ሰነዶች ይፈራረሳሉ፣ እውነትም ትቀበራለች፡፡

ጭራቁን የሚያስፈራው አንድ ነገር ብቻ ነው፤ እርሱም ብርሃን ነው፡፡ የሕሊና ብርሃንና የግልጽነት ጨረር ሲነካው፣ ያ የሚያብረቀርቀው አረንጓዴ ዓይኑ ይጠፋል፡፡ ያን ጊዜ ጭራቁ በላያቸው ላይ የቆመባቸው ሰዎችም ራቁታቸውን ይቀራሉ፡፡ የወጉ መጨረሻ የሚነግረን ግን ይሄንኑ ነው፦ ሙስና አረንጓዴ ዓይን ያለው ጭራቅ (The Green-Eyed Monster) ቢሆንም፣ የሚመገበው ግን የእኛን ዝምታና የእኛን”ምን አገባኝ‘ባይነት ነው፡፡ ይህ ጭራቅ እንዳያድግ ሰንሰለቱ እንዲበጠስ የእያንዳንዳችን ጽናትና ግልጸኝነት፣ ሰይፉ ደግሞ የታማኝነት ብርሃን ነው፡፡